# ቆሪጥ ያዳቆነው

ሆራ ላይ ተጠምቆ ፣ አድገቱ ቢሸፍቱ
ክህደት የተጣባው ፣ ገና ከውልደቱ
አፈንግጦ የወጣ ፣ በደርግ ከሸፈቱ
የበረከት ሎሌ ፣ የጉምቱ ሕውሃቱ
ቅንጅትን ከድቶ ፣ ሺዎችን ካስመቱ
ዛሬም በኢዜማ ፣ ታየ ምልክቱ
አቋም የለሽ ባዶ ፣ የከንቱዎች ከንቱ ።

አቅሙን የማያውቅ ፣ እንደሌለው ዋጋ
ባህሪው ያራዊት ፣ ልክ እንደ ጅብ መንጋ
ዛር ለቆመላቸው ፣ ቢልም ጠጋ ጣጋ
አልሰምርልህ ያለው ፣ ቀን ከሌት ቢተጋ
በጥፍሩ ቢቆምም ፣ ስልጣንን ፍለጋ
ወንበር እንቢኝ አለች ፣ ለብርሃኑ ነጋ ።

አርጅቶም አይማር ፣ ሁሌም ታጥቦ ጭቃ
በደመ ነፍስ ተጓዥ ፣ ከእንቅልፉ የማይነቃ
አፉ ብቻ የቀረ ፣ ወኔ ቢስ ቦቅቧቃ
እየተራመደ ፣ ሁሌም በሰው ጫንቃ
እራሱን አዋርዶ ፣ ወገን የሚያስጠቃ
ዘወትር አጎብዳጅ ፣ የጠባብ ጠበቃ
መካድ የለመደ ፣ በጠፍ በጨረቃ
ሊነገር ይገባል ፣ ካሁን ወዲያ ይብቃ ።

ሁሌ መንሸራተት ፣ እንደ ተልባ ስፍር
አይኑን በጨው ታጥቦ ፣ ጭራሽ የማያፍር
አገር የሚያውቀውን ፣ ያደባባይ ሚስጥር
ዋስ ጠበቃ መሆን ፣ ለአብይ ምስክር
ድንጋይ ዳቦ ያሰኛል ፣ አይ የስልጣን ፍቅር
ምነው እናትህ ሆድ ፣ ሽል እንዳለህ ብትቀር ።

የውሻ ባህሪ ፣ ለትፋት መመለስ
ስልጣን እያሰሉ ፣ ዘወትር መልከስከስ
ነውር አይሰለቸው ፣ ተምሮም አጋሰስ
ለገበያ ቀርቦ ፣ ካሉት ሁሉ መርከስ
ውርደት ኒሻን ሆኖት ፣ የሚያወጣ ደንደስ
ቆሪጥ ያዳቆነው ፣ የቢሸፍቱው መንፈስ
ብርሃኑ ብቻ ነው ፣ ባገር የሚጠቀስ ።

ታዛቢው

September 6, 2020